የምዕራብ ኒው ዮርክ የሞያ ደህንነትና ጤንነት ካውንስል



# COVID-19

# የሠራተኛ ጥቅሞች መመሪያ መጽሐፍ

wny
cosh

## ማውጫ


የሀላፊነት አለመመልከት 1

ስለ WNYCOSH 1

የCOVID-19 የሠራተኛ ጥቅም ፕሮግራሞች አጭር ማጠቃለያ 2

የሥራ አጥነት ድጋፍ 3

የኒው ዮርክ እስቴት (NYS) የሥራ አጥነትና የCares Act 3

ተከፋይ የሕመም ፈቃድ 6

የኒው ዮርክ እስቴት (NYS) COVID-19 ተከፋይ የሕመም ፈቃድ 6

የፌዴራል ተከፋይ የሕመም ፈቃድ (የቤተሰቦች የመጀመሪያው የኰሮና ቫይረስ ምላሽ ውሳኔ የሠራተኛ ተከፋይ ፈቃዶች መብት (FFCRA)) 8

ተከፋይ የቤተሰብ ፈቃድ 10

የኒው ዮርክ እስቴት (NYS) ተከፋይ የቤተሰብ ፈቃድ 10

ልጅዎ ወይም የልጅዎ ትምህርት ቤት እንዲገለል ከተደረገ የቤተሰብ እንክብካቤ 10

የፌዴራል ተከፋይ የተስፋፋ የቤተሰብና የሕክምና ፈቃድ (የቤተሰቦች የመጀመሪያው የኰሮና ቫይረስ ምላሽ ውሳኔ የሠራተኛ ተከፋይ ፈቃዶች መብት (FFCRA)) 14

የፌዴራል ማነቃቂያ (stimulus) ቼኮች 16

አደገኛ ሥራን ያለመሥራት መብት 17

የተጣመረ እንቅስቃሴ 17

የOSHA አደገኛ ሥራን ያለመቀበል መብት 17

ዋቢ 183

የሀላፊነት አለመመልከት

የምዕራብ ኒው ዮርክ የሞያ ደህንነትና ጤንነት ካውንስል (WNYCOSH) የግብረ ሰናይ ድርጅት ነው የዚህ መጽሐፍ አላማ ለመረጃነት እንዲያገለግል ብቻ ነው ስለዚህ እንደ ሕጋዊ ምክር ወይም እንደ ኦፊሴላዊ የመንግሥት ሠነድ ተደርጎ እንዳይወሰድ እናሳስባለን ይህ መረጃ በመንግሥት በኩል የተሰጡ ኦፊሴላዊ መግለጫዎችን የመሻር ዓላማ የለውም በዚህ መጽሔት ውስጥ የተካተቱት ፕሮግራሞች ገና በመተግበር ላይ ያሉ ስለሆኑ ሊቀየሩ የሚችሉበት ሁኔታም ይኖራል ስህተቶች ቢኖሩ ሆን ተብለው የተደረጉ እንዳልሆኑ ይታወቅልን እንዲሁም WNYCOSH በመጽሐፉ ዝግጅት ላይ በተቻለ መጠን ከሚመለከታቸው የመንግሥት ኤጀንሲዎች ማብራሪያዎችን ለማግኘት ብርቱ ጥረት አድርጓል ጥያቄዎችና ማረሚያዎች ካላችሁና ማብራሪያዎች የምትፈልጉ ከሆነ እባካችሁ የWNYCOSHን የሠራተኞች ማዕከልን የስልክ መስመር በመጠቀም በ (716) 206-3550 ደውላችሁ አግኙን

WNYCOSH የዚህን ሰነድ ማንኛውንም ትርጉሞች ትክክለኛነት ዋስትና ለመስጠት አይችልም ከታመኑ የሕብረተሰቡ አጋሮች ጋራ እየሰራን ስለሆነና በአጭር ጊዜ ውስጥ መጠናቀቅ ስለነበረበት የትርጓሜውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ምንም መንገድ አልነበረንም

## ስለ WNYCOSH

WNYCOSH የተመሠረተው በሠራተኛ በአካባቢና በሕዝብ የጤና ጥበቃ ተሚጋቾች በ1979 ዓ.ም. ነው ከ300 በላይ ሰዎች የተሳተፉበት መሥራች ጉባዔው የተደራጀው በ Love Canal እና በ Niagara Falls, NY በነበረው የጉድይር ፋብሪካ (Goodyear plant) ስለነበረው ለመርዝ ተጋላጭነትና የተያያዙ ሕመሞችን በተመለከተ የሕዝቡን ግንዛቤ ከፍ ለማድረግ ያሰበ ነበር ባለፉት 41 ዓመታት WNYCOSH አባሎቹን ከሠራተኛ ማህበሮች (locals) ከጤናና ከደህንነት ተሚጋቾች እንዲሁም ከሕዝብ ጤናና ከሕግ ባለሞያዎች እንዲሁም በሞያ ደህንነትና በጤና ጉዳዮች ላይ ፍላጎት ያላቸው ግለሰቦችን በማካተት መሠረቱን ገንብቷል WNYCOSH በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሠራተኞችን አጠናክሯል ከነዚህም ውስጥ ወጣት ሠራተኞን ስደተኞችን ኢሚግራንት ሠራተኞችን በአነስተኛ ክፍያ የሚተዳደሩ ሠራተኞችንና ለአደጋ በሚያጋልጡ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞችን በሚሠሩባቸው ቦታዎች ውስጥ አደጋዎችን ለመለየት ለማመዛዘንና ለመቆጣጠር እንዲችሉ ቀጥታ ትምህርት በመስጠት ረድቷል
1
WNYCOSH የሎካል የእስቴትና የሃገር መሰባሰቦችን ለመመሥረት የበኩሉን ድጋፍ አድርጓል ለምሳሌ ያህልም የኤኮኖሚ ፍትህ ጥምረት የኒው ዮርክ እስቴት ሠራተኛ - አካባቢ ኔትዎርክ የምዕራብ ኒው ዮርክ (WNY) የፍትሃዊ ገበያ ጥምረት የሞያ ደህንነትና ጤንነት አስተዳደር (OSHA) - የአካባቢ ኔትዎርክና የኒው ዮርክ እስቴት (NYS) ዜሮ ሊፍት ግብረ ሃይልን ረድቶ በዚያውም የሞያ ደህንነትንና ጤንነትን ለመጠበቅና አዳዲስ መመዘኛዎችንም ለማስከበር የበኩሉን አስተዋጽኦ አድርጓል

ስለታሪካችን ተጨማሪ ለማወቅ ከፈለጉ ይህንን ይጫኑ

WNYCOSH
2495 Main Street
Suite 438
Buffalo1, NY 14214
ስልክ: (716) 833-5416
ፋክስ: (716) 833-7507
የተለከከበት ቀን 3/29/20 የተከለሰበት ቀን 4/13/20

# የCOVID-19 የሠራተኛ ጥቅም ፕሮግራሞች አጭር ማጠቃለያ

| ፕሮግራም | ጥቅሞች | ብቁነት | ጠቃሚ ጐን | ጐጂ ጐን |
|---|---|---|---|---|
| የሥራአጥነት ድጋፍ | ለሠራተኞች ድጋፍ ለመስጠት እስከ 39 ሣምንቶች ድረስ ይከፍላል ከፍተኛው ክፍያ $504/በሣምንት ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ $600/በሣምንት እስከ 18 ሣምንቶች ይከፍላል ተጨማሪው የ $600 ክፍያ በ 7/31/20 ያቆማል ተጨማሪዎቹ 13 ሣምንቶች ደግሞ በ 12/31/20 ያበቃሉ | ይህንን ፕሮግራም ለመጠቀም የሚችሉት ከሥራቸው የተገለሉ ሠራተኞች ወደ ሥራቸው እንዳይገቡ የተደረጉ ሠራተኞች ወይም ደግሞ ፈጽመው የተባረሩ መሆን አለባቸው ይህ ፕሮግራም የራሳቸውን ሥራ የሚሠሩትን እና የግል ተቋራጮችን እንዲሁም ሥራ ለመጀመር ታቅደው የነበሩና በ COVID19 ምክንያት ሥራ ለመጀመር ያልቻሉትንም ያጠቃልላል | የኒው ዮርክ እስቴት (NYS) የ 7 ቀኖች የመጠበቂያ ጊዜውን አንስቶታል የ CARES Act የተቀጣሪ ሠራተኞችን ትርጓሜ አስፍቶ ተጨማሪ $600/በሣምንት የሚሰጥ ድጋፍን ለ 18 ሣምንቶች እና ተጨማሪ የ 13 ሣምንቶች የሥራ አጥነትን ለመቋቋም የሚደግፉ ጥቅሞች ሰጥቷል | |
| የኒው ዮርክ እስቴት (NYS) ተከፋይ የሕመም ጊዜ | እስከ 80 ሰዓቶች የሕመም ጊዜን ይከፍላል ይህ እንዴት እንደሚከፈል የድርጅቱ መጠን ይወስነዋል | ሠራተኛው በካውንቲው የጤና ክፍል (DOH) በግድ ወይም ለቅድመ ጥንቃቄ ሲባል ከሰው እንዲገለል የሚያደርገው ትዕዛዝ እንዲኖረው ያስፈልጋል | ለሁሉም ሠራተኞች ጥቅም ይሰጣል ከአሠሪው መጥን ጋር አይያያዝም | ከ 100 ሠራተኞች በታች ላላቸው አሠሪዎች የጥቅም ማመልከቻዎቹን ለየብቻ ማስገባት ያስፈልጋል በጣም የሚወስን ነው |
| የፌዴራል ተከፋይ የሕመም ጊዜ | የሚፈለገውን ለሚያሟሉ ሠራተኞች እስከ 80 ሰዓቶች የሕመም ጊዜን በቀጣሪዎች በኩል በቀጥታ ይከፈላል | ከ 50 እስከ 500 ሠራተኞች ባላቸው ድርጅቶች ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞች ይጠቀማሉ | ይህን ጥቅም ለማግኘት ማመልከት የለብዎትም ጥቅሞቹ የሚከፈሉት በቀጥታ በአሠሪዎቹ በኩል ብቻ ነው | ከ 50 በታችና ከ 500 በላይ ሠራተኞች ባላቸው ድርጅቶች ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞችን አይሸፍንም |
| የኒው ዮርክ እስቴት (NYS) ተከፋይ የልጅ የሕመም ፈቃድ | እራሱ የተገለለ ልጅ ወይም ትምህርት ቤቱ የተገለለበት ልጅ ያለው ወላጅ ከልጁ ጋር እቤቱ እንዲቆይ ይፈቅዳል | በአሁኑ ጊዜ ለልጁ ወይም ለትምህርት ቤቱ እንዲገለሉ ትእዛዝ የተሰጠበት ማስረጃ ያስፈልጋል | ልጆቻቸውን ለመንከባከብ የሚገደዱ ሠራተኞች የማግለያ ጊዜው እስከሚያበቃበት ጊዜ ድረስ ይሸፈናሉ | በአሁኑ ጊዜ የኒው ዮርክ እስቴት (NYS) ተከፋይ የልጅ የሕመም ፈቃድ በካውንቲው የጤና ክፍል (DOH) የማግለያ ተእዛዝ ሲኖር ብቻ ነው |
| የኒው ዮርክ እስቴት (NYS) ተከፋይ የቤተሰብ ፈቃድ | የቤተሰቡን አባል ከመደበኛ ክፍያቸው እስከ 60% እየተከፈለ ለአስር ሣምንቶች እንዲንከባክቡ ይፈቅዳል | የቤተሰብዎ አባል ከባድ የጤና ችግር ካለበትና ይህም ፈቃድ ባለው የጤና እንክብካቤ ሰጪ አካል የተረጋገጠ ከሆነ ለኒው ዮርክ እስቴት (NYS) ተከፋይ የቤተሰብ ፈቃድ ለማግኘት ይችላሉ | ከ COVID-19 ጋር የተያያዘ መሆን አይኖርበትም | ከፌዴራል ፕሮግራሙ በታች ነው የሚከፍለው |
| የፌዴራል ተከፋይ የቤተሰብ ፈቃድ | የቤትሰቡን አባል እስከ 10 ሣምንቶች ድረስ ከ COVID-19 ጋር በተያያዘ ለታመመ ቤተሰብ እንዲንከባከቡ ይፈቅዳል | ከ COVID-19 ጋር በተያያዘ ለግለሰብ ወይም ልጅ እንክብካቤ በ COVID-19 ምክንያት የተዘጉ ትምህርት ቤቶችንም ያጠቃልላል | እስከ 2/3 ኛውን የሣምንቱን ደሞዝ ይከፍላል ለቅድመ ጥንቃቄ ሲባል የተዘጉ ትምህርት ቤቶችንም ያጠቃልላል | ከ COVID-19 ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ብቻ መሆኑ |
| የፌዴራል የማነቃቂያ (Stimulus) ቼኮች | የአንድ ጊዜ ክፍያ የሆኑ $1200 እና $500 ከ 16 ዓመት በታች ለሆኑና ጥገኛ ለሆኑ ልጆች | የ 2018, 2019 ታክስ መክፈልና ገቢዎ ደግሞ ከ $75,000/ለግለሰብ እና ከ $150,000/ለባለትዳሮች በታች መሆን ይኖርበታል | ይህ ክፍያ ከታክስ ነጻ የሆነ መሆኑና ብዙዎቹ ታክስ ከፋዮች የማነቃቂያ (stimulus) ክፍያውን በቀጥታ የሚያገኙ መሆኑ | ታክስ የማይከፍሉ ሰዎች የማነቃቂያውን (stimulus) ክፍያ ለማግኘት ያስቸግራቸዋል |

## መግቢያ

የኰሮና ቫይርስ (COVID-19) አደጋ ከተከሰተ ወዲህ ብዙ የንግድ ተቋሞች በመዘጋታቸው ምክንያት ብዙ ስዎች እራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ለመደገፍ አዳግቷቸዋል  የኒው ዮርክ እስቴት (NYS) በማህበረሰቡ ውስጥ የቫይረሱን ስርጭት ለመወሰንና የማህበራዊ መራራቅን በማበረታታት የቫይረሱን ስርጭት ለማቆም ለሕይወት አስፈላጊ ያልሆኑ የንግድ ተቋሞችን እንዲዘጉ አድርጓል የእስቴቱና የፌዴራል መንግሥቶች ፕሮግራሞችን በመፍጠርና ያሉትን በማስፋፋት የተቋሞቹ መዘጋት የሚያመጣውን የገንዘብ ጫና ለመወሰንና የገንዘብ እርዳታ ለመስጠት እርምጃዎች ወስደዋል ከዚህ በታች እባክዎ በCOVID-19 ወረርሽኝ ምክንያት ለተጐዱ ዕርዳታ ከሚሰጡ ፕሮግራሞች ውስጥ አንዳንዶቹን ይመልከቱ እባካችሁ ከአጭበርባሪዎች ተጥንቀቁ በእነዚህ ፕሮግራሞች ውስጥ ለመሳተፍ ምንም አይነት ክፍያ መክፈል አያስፈልግም የቅድሚያ ክፍያ ወይም ሌላ የገንዘብ ክፍያ መስጠትም አያስፈልግም ማንኛውም ሰው አገልግሎቱን ለማግኘት የገንዘብ ክፍያ ከጠየቀዎት ይህ በእርግጠኛነት እርስዎን አጭበርብሮ ለራሱ ሊጠቀምብዎት የሚፈልግ ሰው ነው

ብዙዎቹ የኦንላይን (Online) አገልግሎቶች የሚገኙት በተወሰኑ ቋንቋዎች ብቻ ነው የሚከተሉት የኢሚግራንቶች አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ማንኛውንም በአሜሪካን ውስጥ ለመሥራት ፈቃድ ያለውን ሰው ይረዳሉ

| | |
|---|---|
| ጆርኒስ ኤንድ የስደተኛ አገልግሎቶች (Journey's End Refugee Services )<br>የተወካዩ ስም: ሃሰን አሊሻቂ<br>ስልክ ቁጥር: (716) 882-4963 ኤክስ. 218<br>ኢሜይል: halishaqi@jersbuffalo.org | የበፋሎ ኢንተርናሽናል ኢንስቲትዩት (International Institute of Buffalo)<br>የተወካዩ ስም: ዜቪየር ሜዲና<br>ስልክ ቁጥር: (718) 614-5806<br>ኢሜይል: |
| የበፋሎ ጁዊሽ በተሰብ አገልግሎት (Jewish Family Services of Buffalo)<br>የተወካዩ ስም: ዳርዊን ኒውኩርክ<br>ስልክ ቁጥር:(716) 390-4044<br>ኢሜይል: | የበፋሎ ካቶሊክ በጎአድራጊዎች (Catholic Charities of Buffalo)<br>የኢሚግሬሽንና የስደተኞች ዕርዳታ<br>የቅጥር ክፍል<br>ስልክ ቁጥር: (716) 842-0270<br>ኢሜይል: ecs@ccwny.org |
| | |

## የሥራ አጥነት ድጋፍ

### የኒው ዮርክ እስቴት (NYS) የሥራ አጥነትና የCares Act

የሥራ አጥነት ድጋፍ (Unemployment) በአሠሪዎች የሚከፈል ሆኖ ሠራተኞች ያለራሳቸው ጥፋት ከሥራ ሲወገዱ ወደ ሥራ እንዳይገቡ ሲከለከሉና ከሥራ ጨርሰው ሲባረሩ ጥቅምና ድጋፍ የሚሰጥ የኢንሹራንስ ፕሮግራም ነው

## እንዴት አድርገው የሚፈለገውን ማሟላት እንደሚችሉ

በኒው ዮርክ እስቴት (NYS) የሠራተኛ ሕግ መሠረት ድጋፍ ለማግኘት ከሥራ ከመወገድዎ ወደሥራ ኢንዳይገቡ ከመከልከልዎና ከሥራዎ ከመባረርዎ በፊት ለስድስት ወሮች ወይም ደግሞ ለ 2 ሩብ ዓመት መሥራት ይኖርብዎታል ብዙውን ጊዜ ለሥራ አጥነት ድጋፍ የሚሰጥዎት መጠን የሚሰላው ከፍተኛ ገቢ ያገኙበትን ሩብ ዓምት በ26 በማካፈል ነው ለኒው ዮርክ እስቴት (NYS) ከፍተኛው የሥራ አጥነት ድጋፍ መጠን $504/በሣምንት ነው አመልካቾች እስከ 26 ሣምንቶች ድረስ ዕርዳታ ለማግኘት ይችላሉ ሥራዎ ከሙሉ ሰዓት ሠራተኛነት ወደ ትርፍ ሥራ ሠራተኛነት ከተቀየረና ገቢዎ ከ $504/በሣምንት በታች እስከሆነ ድረስ የሥራ አጥነት ድጋፍ በከፊል ለመጠየቅ ይችላሉ ከላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች ባያሟሉም እንኳን በ Cares Act የሚያሟሉ ከሆነ ለሥራ አጥነት ድጋፍ በኒው ዮርክ እስቴት (NYS) ፖርታል (Portal) በኩል ወይም በስልክ ለማመልከት ይችላሉ የፌዴራሉ የ Cares Act በተጨማሪ የማይቀየየር $600/በሣምንት በእስቴቱ ዕርዳታ ላይ ይጨመርልዎታል ይህንን ተጨማሪ ዕርዳታ ለማግኘት የሚችሉበት ወቅት የኒው ዮርክ እስቴት (NYS) ፕሮግራሙን በኦፊሴል የገባበት ጊዜ ይሆናል ይህ ለሥራ አጥነት ዕርዳታ ሲመዘገቡ በሚያገኙት ዕርዳታ ላይ በቀጥታ ይጨምራል

ይህንን ተጨማሪ ድጋፍ እስከ 18 ሣምንቶች ድረስ ለመጠየቅ ይቻላል ነገር ግን ይህ ድጋፍ በ July 31, 2020 ያቆማል የ Cares Act ደግሞ ለተጨማሪ 13 ሣምንቶች የሥራ አጥነት ድጋፍ የእርስዎ እስቴት በሚሰጥዎ ስሌት መጠን በጠቅላላው ለ 39 ሣምንቶች ይሰጥዎታል ለዚህ ብቁ ሆኖ ለመገኘት በትንሹ $2600/በሩብ ዓመት ማግኘት ይኖርብዎታል በCOVID-19 ወረርሺኝ ምክንያት የኒው ዮርክ እስቴት (NYS) የነበረውን የ 7 ቀኖች የመጠበቂያ ጊዜ አንስቶታል

በተጨማሪ የ Cares Act የሠራተኛን ትርጉም ስላስፋፋው በራሳቸው ሥራ የሚተዳደሩ የግል ተቋራጮች ሆነው የሚሠሩና ሥራቸውን ለመጀመር ተዘጋጅተው ቀጠሮ ላይ የነበሩና በአለው ሁኔታ ምክንያት አዲሱን ሥራቸውን ለመጀመር ያልቻሉትንም ያጠቃልላል  የ Cares Act በCOVID-19 ምክንያት ለተነኩ ሠራተኞች የሥራ አጥነትን ድጋፍ ይሰጣል ይህ ሥራቸውንም እንዲለቁ የተደረጉትን ይጨምራል ይህ ከቤታቸው ሆነው መሥራት የሚችሉትን ወይም ደግሞ ሥራ ሳይሰሩ እየተከፈላቸው በፈቃድ ላይ ያሉ ሠራተኞችን አይሸፍንም

## እንዴት ማመልከት እንደሚችሉ

ኦንላይን (Online) ለማመልከት ይህን ድህረ ገጽ ይጎብኙ https://on.ny.gov/2UbvHd6 እና የራስዎን የ "NY.gov" አካውንት ይፍጠሩ ነገር ግን ከዚህ ቀደም የተጠቀሙበት የራስዎ የ NY.gov አካውንት ካለዎት ወደ አካውንትዎ ለመግባት ይችላሉ (login)  የኒው ዮርክ እስቴት (NYS) የሥራ አጥነት ድጋፍ ዌብሳይት (website) በጣም ከፍተኛ የሆነ የተጠቃሚ ትራፊክ ስላለው መልሱ በጣም ሊዘገይ እንድሚችልና ወይም ደግሞ ዌብሳይቱ (website) ጨርሶ ሊበላሽ አንደሚችል ከወዲሁ እናስገነዝባለን በጣም ተዕግሥትኛ ሆነው ያለማቋረጥ መሞከር ይኖርብዎታል

በስልክ ለማግኘት 1 (888) 209-8124 ከ 8 AM  እስከ 5 PM ባለው ሰዓት ይደውሉ ለብዙዎቹ የአፕ እስቴት ኢሚግራንት ቋንቋዎች ለ "ሁሉም ሌላ ቋንቋዎች" ብሎ ዕድል የሚሰጠውን አማራጭ ለማግኘት 9 ቁጥርን ይጫኑ ብዙ የስልክ ጥሪዎችን ስለሚያስተናግዱ ለረዥም ጊዜ በስልክ ላይ ሆነው መጠበቅ ይኖርብዎት ይሆናል የጥሪዎችን ብዛት ለመቀነስ በማሰብ የኒው ዮርክ እስቴት የሠራተኛ ክፍል (NYS DOL) የሚከተለውን መመሪያ ለሕዝብ ስጥቷል በዚህም መሠረት የመጨረሻ ስማቸው (Surname) ከ A እስከ F ባለ ፊደል የሚጀምር ሰዎች ሰኞ ቀን እንዲደውሉ  የመጨረሻ ስምዎ (Surname) ከ G እስከ N  ባለ ፊደል የሚጀምር ከሆነ ማክሰኞ ቀን ይደውሉ የመጨረሻ ስምዎ (Surname) ከ O እስከ Z ባለ ፊደል የሚጀምር ከሆነ ረቡዕ እለት ይደውሉ በተሰጠው ቀን ማመልከቻዎን ሳያስገቡ ለእርስዎ የተመደበው ቀን ካመለጠዎት ኀሙስ ዓርብ እና ቅዳሜ ለማመልከት ይችላሉ ማመልከቻዎም ወደኋላ ተመልሶ ባመለከቱበት ሣምንት ከሰኞ ዕለት ጀምሮ ይመዘገባል  የጥሪዎች ብዛት እጅግ በጣም ከፍተኛ ስለሚሆንና በስልክ የሚያስተናግድዎትን ሰው ከማነጋገርዎ በፊት ብዛት ያላቸው በእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚሰጡና የተቀዱ ማስታወቂያዎች እንዳሉ እባክዎን ይገንዘቡ መልስ በሚያገኙበት ሰዓት ኢንተርፕሬተር

“Interpreter” ይበሉና የእርስዎን ቋንቋ የእንግሊዝኛ ስም ይናገሩና በዚህ ጊዜ ኦፕሬትሩ አስተርጓሚ ማግኘት እንዲችሉና በስልክ እርዳታ እንዲያገኙ ሊያደርግ ይችላል

## ማመልከቻዎን ለማስገባት የሚያስፈልግዎት

• የሶሻል ሴኪዩሪቲ ቁጥርዎ
• የመንጃ ፈቃድዎ ወይም የተሽከርካሪ መታወቂያ ካርድ ቁጥርዎ (ከእነዚህ አንዳቸው ካለዎት)
• ሙሉ የፖስታ አድራሻዎና zip ኮድ
• የኒው ዮርክ እስቴት (NYS) የሥራ አጥነት እርዳታ ክፍል ከ ሰኞ እስከ ዓርብ ከ 8 AM አስከ 5 PM ሊያገኝዎት የሚችልበት የስልክ ቁጥር
• የውጪ አገር ዜጎች የነዋሪነት ፈቃድ ካርድ ቁጥር (የአሜሪካን ዜግነት ከሌለዎትና ካርዱ ካለዎት)
• ባለፉት 18 ውራት ውስጥ የሰሩባቸው የቀጣሪ ድርጅቶች ስምና አድራሻ በሌላ እስቴቶች ውስጥ ያሉትንም ጭምር የቀጣሪ ድርጅትዎ የምዝገባ ቁጥር ወይም የፌዴራል ቀጣሪ ድርጅት የምዝገባ ቁጥር (FEIN) በቅርብ ጊዜ የሠሩበት የፌዴራል ቀጣሪ ድርጅት የፌዴራል የምዝገባ ቁጥር (FEIN) በ W-2 ላይና ብዙውን ግዜም በደሞዝ ክፍያ ማስረጃ ወረቀት ላይም ይገኛል

## እንዴት ክፍያዎን እንደሚያገኙ

የሥራ አጥነት ድጋፍ ማካካሻ ክፍያዎ ወይ በቀጥታ በባንክዎ በኩል ወደ እርስዎ አካውንት ውስጥ ያስገቡልዎታል ወይንም ደግሞ የሠራተኛ ክፍል (DOL) በሚሰጠው የዴቢት ካርድ (Debit card) በኩል ይሆናል የሥራ አጥነት መደገፊያ ክፍያዎች ታክስ እንደሚከፈልባቸው እባክዎ ያስተውሉ በአሁኑ ወቅት ለሠራተኞች በCares Act በኩል የሚያገኙት የ $600/በሣምንት ክፍያ ታክስ የሚከፈልበት መሆኑ በግልጽ አልታወቀም ተጨማሪውን $600 የ Medicaid ወይም CHIP ብቃትን ለመወሰኛ ይጠቀሙበታል

## ተከፋይ የሕመም ፈቃድ

## የኒው ዮርክ እስቴት (NYS) COVID-19 ተከፋይ የሕመም ፈቃድ

የኒው ዮርክ እስቴት (NYS) ተከፋይ የሕመም ፈቃድ አዲስ የመጣ ሕግ ሲሆን የሚጠቅመውም በCOVID-19 ወረርሽኝ ምክንያት ሠራተኞች በግዳጅ ወይም ለቅድመ ጥንቃቄ ሲባል ቢገለሉ የሥራ ዋስትናና ገቢ እንዲያገኙ የሚያደርግ ነው

አነስተኛ ቀጣሪዎች ከ 10 ሠራተኞች በታች ያላቸውና ከ $1,000,000 በታች የተጣራ ገቢ ያላቸው የንግድ ድርጅቶች

እነዚህ ድርጅቶች ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞች ለኒው ዮርክ እስቴት (NYS) ክፍያ ያለው የሕመም ፈቃድ ብቁ አይደሉም ነገር ግን የኒው ዮርክ እስቴትን (NYS) ተከፋይ የቤተሰብ ፈቃድ እና የኒው ዮርክ እስቴትን (NYS) የአካል ጉዳተኛ ጥቅሞችን በማጣመር በነዚህ በኩል ሙሉ ክፍያቸውን ማግኘት ይችላሉ

መካከለኛ ቀጣሪዎች ከ 11 እስከ 99 ሠራተኞች ያላቸውና የተጣራ ገቢያቸው ከ $1,000,000 በላይ የሆኑ የንግድ ድርጅቶች

እነዚህ ድርጅቶች ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞች የ 5 ቀኖች የኒው ዮርክ እስቴትን (NYS) ተከፋይ የሕመም ፈቃድ ለመውስድ ይችላሉ ከዚህ በኋላ ደግሞ የኒው ዮርክ እስቴትን (NYS) ተከፋይ የቤተሰብ ፈቃድ እና የኒው ዮርክ እስቴትን (NYS) የአካል ጉዳተኛ ጥቅሞችን በማጣመር እስከ 14 ቀኖች ድረስ ሙሉ ክፍያቸውን ማግኘት ይችላሉ

ትላልቅ ቀጣሪዎች በትንሹ 100 ሠራተኞች ያሉዋቸው የንግድ ድርጅቶችና ሁሉም የመንግሥት ሠራተኞች ጭምር

ቀጣሪዎ ከCOVID-19 ጋር ለተያያዙ ሕመሞች በትንሹ 14 ቀኖች ተከፋይ የሕመም ፈቃድ መስጠት አለበት ይህ በቀጥታ በቀጣሪዎ በኩል ይከፈላል

## እንዴት አድርገው የሚፈለገውን ማሟላት እንደሚችሉ

በኒው ዮርክ እስቴት (NYS) የጤና ክፍል ወይም በአካባቢው (local) የጤና ቦርድ ወይም በሌላ በማንኛውም ሥልጣን በተሰጠው የመንግሥት አካል በግዳጅም ሆነ በቅድመ ጥንቃቄ ምክንያት በCOVID-19 የተነሣ የተሰጠ የመገለል ወይም ለብቻ የመሆን ተእዛዝ ያስፈልጋል ይህ መገለል በ Erie ካውንቲ የጤና ክፍል ወይም ደግሞ በሌላ አግባብ ባለው የመንግሥት አካል መመዝገብ ይኖርበታል

እባክዎ የሚከተለውን ይገንዘቡ የErie ካውንቲ የጤና ክፍል የማግለያ ተእዛዝ የሚሰጠው በCOVID-19 የላቦራቶሪ ማጣሪያ አዎንታዊ ውጤት ለተገኘባቸው ብቻ ነው ከጤና ክፍሉ የአስገዳጅ የመገለያ ውሳኔ ወዲያውኑ ካላገኙ እርሶን በሕክምና ከረዳዎትና ፈቃድ ካለው የጤና ባለሞያ የሚያገኙትን ለመገለል ብቁ መሆንዎን የሚያረጋግጥ አስረጂ ሠነድ ሊያስገቡ ይችላሉ (ይህ በቀላሉ የዶክተር ማስታወሻ ሰነድ ማለት ነው) የክፍያ ጥያቄዎን ለማስፈጸም በጤና ኢንሹራንስዎ በኩል አድርገው በአካባቢው የጤና ክፍል (DOH) በኩል ደግሞ 30 ቀኖች በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ ክትትል ያድርጉ ለግለላ ብቁ የሚያደርገው የCOVID-19 የላቦራቶሪ ማጣሪያ አዎንታዊ ውጤት ወይም COVID-19 እንዳለበት ከተረጋገጠ ሰው ጋር ግንኙነት መኖር ወይም በCOVID-19 ማሳሰቢያ መሠረት በ2ኛ በ3ኛ ወይም በ4ኛ ደረጃ ከተመደቡ አገሮች ተመልሰው ገብተው ከሆነ ነው የErie ካውንቲ የጤና ክፍል (DOH) ስለCOVID-19 በቀጥታ የስልክ መስመር በሚሰጠው መረጃ መሠረት ይህ መመዘኛ በ 4/2/20 አነስተኛ ገዳቢ የሆነውን ለተከፋይ የሕመም ፈቃድና ለተከፋይ የቤተሰብ ፈቃድ የሚወጣ የፌዴራል መመሪያን ለማንጸባረቅ ሲባል ሊቀየር ይችላል

የትኞቹ አገሮች የ2ኛ የ3ኛ ወይም የ4ኛ ደረጃ ማሳሰቢያ የተሰጠባቸው እንደሆኑ ለማወቅ CDC የሚሰጠውን መረጃ እዚህ ይመልከቱ https://bit.ly/2wAdvRy

## እንዴት ክፍያዎን እንደሚያገኙ

ብዙውን ጊዜ ኢንሹራንሱ የሚያገኙትን ጥቅም የክፍያ ጥያቄዎን በተቀበለ በ18 ቀኖች ውስጥ ወይ ይከፍልዎታል ወይንም ደግሞ ክፍያው አይገባዎትም በሚል መልስ ይሰጥዎታል ኢንሹራንስዎ ክፍያውን የሚሰጥበትን አማራጮች ሊያቀርብልዎት ይችላል ለምሳሌ በቀጥታ በባንክዎ አካውንት ውስጥ በማስገባት በዴቢት ካርድ (Debit card) ወይንም ደግሞ የወረቀት ቼክ በመስጠት ይሆናል አሠሪዎ ከ 100 ሠራተኞች በላይ ያለው ከሆነ ክፍያ ያለው የሕመም ፈቃድ ለማግኘት ማመልከት የለብዎትም ይህ በቀጥታ ከደሞዝዎ ጋር እንደሌላው ክፍያ ይከፈልዎታል

## እንዴት እንድሚያመለክቱ

ከመካከለኛ እና ከትልልቅ አሠሪዎች የተከፋይ የሕመም ፈቃድ ቀኖች የሚገባዎት ከሆነ እነዚህ የሕመም ቀኖች በቀጥታ በአሠሪው በኩል የሚከፈሉ ስለሆነ ይህንን ክፍያ ለማግኘት እርስዎ ማመልከት አይኖርብዎትም

ለአነስተኛ ወይም ለመካከለኛ ድርጅቶች የሚስሩ ከሆነ እና ከተገለሉ ወይም የአምስቱን ቀኖች የኒው ዮርክ እስቴት (NYS) ተከፋይ የሕመም ፈቃድ ከተጠቀሙ በኋላ የኒው ዮርክ እስቴትን (NYS) ተከፋይ የቤተሰብ ፈቃድ እና የኒው ዮርክ እስቴትን (NYS) የአካል ጉዳተኛ ጥቅሞችን የሚከተለውን ፎርም ሞልተው ለማመልከት ይችላሉ https://on.ny.gov/2xoPBYV

ይህንን ፎርም ለመሙላት የቋንቋ እገዛ የሚያስፈልግዎ ከሆነ በስልክ 1 (844) 337-6303 ይደውሉና ከሚሰጡት አማራጮች ውስጥ 1 የሚለውን አማራጭ ይጫኑ ክዚያ ቀጥለው ደግሞ 5 የሚለውን አማራጭ ይጫኑና ኦፐሬተሩ በመለሰልዎት ጊዜ ኢንተርፕሬተር "Interpreter" በማለትና የእርዎን ቋንቋ የእንግሊዝኛ ስም በመናገር አስተርጓሚ ይጠይቁ ኦፐሬተሩን ለማነጋገር ለረዥም ጊዜ በስልክ ላይ ሆነው መጠበቅ ያለብዎት ሲሆን በሚጠብቁበትም ጊዜ ብዛት ያላቸው በእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚሰጡ ማስታወቂያዎች እንዳሉ እባክዎን ይገንዘቡ

ከላይ የተጠቀሱትን ፎርሞች በሚሞሉበት ጊዜ በፎርም PFL-1 ላይ ያሉትን 11ኛውንና 12ኛውን ጥያቄዎች አይመልሷቸው ባዶ አድርገው ይተዋቸው እነዚህ ጥያቄዎች በዚያው በ ፒዲኤፍ (pdf) ፋይል ውስጥ ቀጥሎ በሚመጣው በSCOVID-19 ክፍል ውስጥ ተሸፍነዋል የሞሉትን የPFL-1 ፎርምዎን ቅጂ ለራስዎ ያስቀሩ ድንገት አሰሪዎ ለእርስዎ የማይመልስልዎት ቢሆን ያገለግልዎታል  የተሞላውን ፎርም ለአሰሪዎ ይላኩ አሰሪዎ ፎርሙን በተቀበለ በ3 የሥራ ቀኖች ውስጥ የመመለስ ግዴታ አለበት

በመጨረሻም ፎርምዎን ለአሰሪዎችና ለሠራተኞች አካካሽ መድን ድርጅት ይላኩ አግኝተዋቸው ማመልከቻውን በኤሌክትሮኒክ መንገድ ይቀበሉ እንደሆነ ለማጣራት ይችላሉ የማይቀበሉ ከሆነ ግን በፖስታ ቤት በኩል መላክ ይኖርብዎታል  የአሰሪና የሠራተኞች ማካካሻ መድን ድርጅትዎን ለማግኘት የሚፈልጉ ከሆነ ከዚህ በታች ያለውን ማገናኛ ይጫኑ (ብዙ ገጾች ላይ መጫን ይኖርብዎታል) https://on.ny.gov/2QK1KP5

የአሰሪዎን  የመድን ድርጅት ለማግኘት ካልቻሉ የተከፋይ የበተሰብ የእገዛ የስልክ መስመር ላይ ዕርዳታ ለማግኘት በ 1 (844) 337-6303 ይደውሉና ከሚሰጡት አማራጮች 1 የሚለውን አማራጭ ይጫኑ ክዚያ ቀጥለው ደግሞ 5 የሚለውን አማራጭ ይጫኑ ኦፐሬተሩ በመለሰልዎት ጊዜ ኢንተርፕሬተር "Interpreter" በማለትና የእርዎን ቋንቋ የእንግሊዝኛ ስም በመናገር አስተርጓሚ ይጠይቁ ኦፐሬተሩን ለማነጋገር ለረዥም ጊዜ በስልክ ላይ ሆነው መጠበቅና በሚጠብቁበትም ጊዜ በእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚሰጡ በርካታ ማስታወቂያዎች እንደሚኖሩ እባክዎን ይገንዘቡ የእገዛውን የስልክ መስመር ከሰኞ እስከ ዓርብ ከ 8:30 AM  አስከ 4:30 PM ለማግኘት ይችላሉ

አሰሪዎ የመድን ሽፋን እንደሌለው የሚያምኑ ከሆነ የተከፋይ የበተሰብ ፈቃድ ጥያቄዎን ለኒው ዮርክ እስቴት (NYS) ሠራተኞች ማካካሻ ቦርድ በሚከተለው አድራሻ መላክ ይችላሉ

NYS Workers' Compensation Board
Paid Family Leave
PO Box 9030,
Endicott, NY 13761-9030

## እንዴት ክፍያዎን እንደሚያገኙ

የመጀመሪያ ክፍያዎን ካገኙ በኋላ ተጨማሪ በየሁለት ሣምንቱ ይደረጋል የመድን ድርጅቱ ክፍያውን እንዴት እንደሚከፍልዎት አማራጮች ሊሰጥዎት ይችላል ለምሳሌ በቀጥታ በባንክዎ አካውንት ውስጥ በማስገባት በዴቢት ካርድ (Debit card) ወይንም ደግሞ የወረቀት ቼክ በመስጠት ሊሆን ይሆናል

እባክዎ ያስተውሉ የተከፋይ የቤተሰብ ፈቃድ ክፍያዎች ታክስ ይከፈልባቸዋል ከነዚህ ጥቅሞች ላይ ለታክስ መክፈያ ተብሎ በቀጥታ የሚያዝ ነገር የለም ነገር ግን ሠራተኞች ይህንን በፈቃደኛነት በራሳቸው አነሳሽነት ለታክስ ተብሎ እንዲቆረጥለት ለመጠየቅ ይችላሉ በዚህ ክፍያ ላይ ያለውን የታክስ ክፍያ በመጨረሻ ላይ ታክስዎን በሚያስገቡበት ጊዜ የመክፈል ኃላፊነት አለብዎት

## የፌዴራል ተከፋይ የሕመም ፈቃድ (የቤተሰቦች የመጀመሪያው የኰሮና ቫይረስ ምላሽ ውሳኔ የሠራተኛ ተከፋይ ፈቃዶች መብት (FFCRA))

FFCRA በ April 1, 2020 በሥራ ላይ ይውላል FFCRA ወደኋላ በመሄድ የሚስተካከል የተከፋይ የሕመም ፈቃድ ጊዜ አይደለም የፌዴራሉ ሕግ ጊዜያዊ ከCOVID-19 ጋር የተዛመደ እስከ 80 ሰዓቶች ድረስ የሚደርስ የመደበኛ ክፍያዎን ስሌት ተከትሎ እስከ ከፍተኛው $511/በቀን ወይም $5,111/በሁለት ሣምንቶች ተከፋይ የሕመም ፈቃድ ይሰጣል ይህ ከ 50 እስከ 500 ሠራተኞች ድረስ በሚያስተናግዱ መሥሪያ ቤቶች ላይ ይሰራል ከ50 ሠራተኞች በታች ያላቸው አሰሪዎች ይህንን ጥቅም ለሠራተኞቻቸው ከመስጠት ነፃ የመሆን ዕድል ይኖራቸው ይሆናል ሠራተኞች ከዚህ ጥቅም ተጠቃሚ ለመሆን በትንሹ ለ 30 ቀኖች ሠራተኛ ሆነው ማገልገል ይኖርባቸዋል

የፌዴራል ተከፋይ የሕመም ፈቃድን ለማግኘት ብቁ ሆኖ ለመገኘት ከሚከተሉት ውስጥ አንዱን ማሟላት ይኖርብዎታል

• በፌዴራል እስቴት ወይም በአካባቢ ከCOVID-19 ጋራ በተያያዙ ምክንያቶች እንዲገለሉ ወይም ለብቻዎ እንዲቆዩ የታዘዙ መሆን ይኖርብዎታል

• በሕክምና እንክብካቤ አገልግሎት ሰጪ እራስዎን ከሰው አግልለው እንዲቆዩ የተነገረዎት ከሆነ

• የCOVID-19 ምልክቶችን ተመልክተው የሕክምና ምርመራ እንዲደረግልዎት እያፈላለጉ ከሆነ

የፌዴራል ተከፋይ የሕመም ፈቃድ ክፍያ በቀጥታ በአሠሪዎ በኩል ይከፈላል ከ 50 እስከ 99 ሠራተኞች ላሉዋቸው አሰሪዎች የፌዴራል ሕጉ ሙሉ የሁለት ሣምንቶች ክፍያዎን ከአሠሪዎ እንዲያገኙ ይደነግጋል ለሁሉም መስፈርቱን የሚያሟሉ ሠራተኞች የፌዴራል ሕጉን ፍላጎት አሟልቶ ለመገኘት በጣም ቀላል ነው ከጤና አገልግሎት ሰጪዎ የሚጻፍ አስረጂ ክፍያውን ለመጠየቅ በቂ ሠነድ ነው

እባክዎ የሚከተለውን ይገንዘቡ  አፈጻጸም ላይ የትኛው ሕግ አሰሪዎችን እንደሚመለከታቸው ብዙ ግራ መጋባት ሊኖር እንደሚችል ይጠበቃል  መልሱ የተጣራ ገቢንና የሠራተኞችን ብዛት የሚመለከት ይሆናል ከ 50 እስከ 500 ሠራተኞችን ለሚያሰራ ድርጅት የፌዴራል ሕጉ የሚመሳሰሉ ጥቅሞችን ነው የሚሰጠው ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ የማመልከት ብቃትን አሟልቶ ለመገኘት ቀላል ነው   የፌዴራል እና የእስቴት መመሪያዎቹን ለአሰሪዎቻችሁ አሳይታችሁ የትኛውን ፕሮግራም ኀላፊነት እንዳለባቸው እንዲገነዘቡ ማድረግ ይኖርባችሁ ይሆናል

የፌዴራል መምሪያ ለአሰሪዎች: https://bit.ly/2UiNVt7
የእስቴት መምሪያ ለአሰሪዎች: https://on.ny.gov/2WMrLkA

## ተከፋይ የቤተሰብ ፈቃድ

## የኒው ዮርክ እስቴት (NYS) ተከፋይ የቤተሰብ ፈቃድ
## ልጅዎ ወይም የልጅዎ ትምህርት ቤት እንዲገለል ከተደረገ

የኒው ዮርክ እስቴት (NYS) ተከፋይ የቤተሰብ ፈቃድ ሕግ እንዲጸድቅ የተደረገው ለCOVID-19 ሲሆን በእርስዎ ጥገኝነት ስር ያለ ልጅዎ (ከ 18 ዓመት በታች የሆነና በእርስዎ ኃላፊነት ስር ያለ ልጅዎ) በግዳጅ ወይም ለቅድመ ጥንቃቄ ሲባል እንዲገለል ወይም ተለይቶ እንዲቀመጥ በኒው ዮርክ እስቴት (NYS) የጤና ክፍል የካውንቲው የጤና ክፍል ወይም በሌላ ሥልጣን በተሰጠው የአካባቢ መንግሥት ሲታዘዝ ይሆናል

## እንዴት አድርገው የሚያስፈልገውን ማሟላት እንደሚችሉ

ልጅዎ በግዳጅ ወይም ለቅድም ጥንቃቄ ሲባል እንዲገለል ወይም ተለይቶ እንዲቀመጥ ወይም የልጅዎ ትምህርት ቤት በCOVID-19 መስፋፋት ምክንያት ተዘግቶ ከሆነ የሚያስፈልገውን ያሟላሉ  የልጅዎ ትምህርት ቤት ማህበራዊ መራራቅን በማምጣት ለመከላከል ሲባል የተዘጋ ከሆነ የኒው ዮርክ እስቴት (NYS) ተከፋይ የቤተሰብ ፈቃድ አይገባዎትም ነገር ግን በFFCRA በኩል ለሚሰጠው የፌዴራሉን የተራዘመ ተከፋይ የቤተሰብ ፈቃድ ሊያሟሉ ይችላሉ (ከዚህ በታች ይመልከቱ)  የኒው ዮርክ እስቴት (NYS) ተከፋይ የቤተሰብ ፈቃድ ከሣምንታዊ ክፍያዎ ላይ በ 60 % ላይ እንዲገደብ የተደረገ ሲሆን (የመጨረሻዎቹ የሥራባቸው 8 ሣምንቶች) ከፍተኛው ክፍያ $840.70/በሣምንት ሆኖ የማግለያው ጊዜ እስከሚያልቅ ድረስ ይሰጣል

እባክዎ የሚከተለውን ይገንዘቡ  የErie ካውንቲ የጤና ክፍል የማግለያ ተእዛዝ  የሚሰጠው በCOVID-19 የላቦራቶሪ ማጣሪያ አዎንታዊ ውጤት ለተገኘባቸው ብቻ ነው  ከጤና ክፍሉ የአስገዳጅ የመገለያ ውሳኔ ወዲያውኑ ካላገኙ እርሶን በሕክምና ከረዳዎትና ፈቃድ ካለው የጤና ባለሞያ የሚያገኙትን ለመገለል ብቁ መሆንዎን የሚያረጋግጥ አስረጂ ሠነድ ሊያስገቡ ይችላሉ (ይህ በቀላሉ የዶክተር ማስታወሻ ሰነድ ማለት ነው)  የክፍያ ጥያቄዎን ለማስፈጸም በጤና ኢንሹራንስዎ በኩል አድርገው በአካባቢው የጤና ክፍል (DOH) በኩል ደግሞ 30 ቀኖች በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ ክትትል ያድርጉ ለግለላ ብቁ የሚያደርገው የCOVID-19 የላቦራቶሪ ማጣሪያ አዎንታዊ ውጤት ወይም COVID-19 እንዳለበት ከተረጋገጠ ሰው ጋር ግንኙነት መኖር ወይም በCOVID-19 ምክንያት በተሰጠ ማሳበቢያ መሠረት በ2ኛ በ3ኛ ወይም በ4ኛ ደረጃ ከተመደቡ አገሮች ተመልሰው ገብተው ከሆነ ነው  የErie ካውንቲ የጤና ክፍል (DOH) ስለCOVID-19 በቀጥታ የስልክ መስመር እንደሰጠው መረጃ ከሆነ ይህ መመዘኛ በ 4/2/20 አነስተኛ ገዳቢ የሆነውን ለተከፋይ የሕመም ፈቃድና ለተከፋይ የቤተሰብ ፈቃድ የሚወጣ የፌዴራል መመሪያን ለማንጸባረቅ ሲባል ሊቀየር ይችላል

## የቤተሰብ እንክብካቤ

ከቤተሰብዎ ውስጥ "ክባድ የጤንነት ችግር" ያለበት ካለ ለተከፋይ የቤተሰብ ፈቃድ ተፈላጊውን ሊያሟሉ ይችላሉ ይህም የቤተሰቡን አባል ለመንከባከብ እስከ 10 ሣምንቶች ይሆናል የኒው ዮርክ እስቴት (NYS) ተከፋይ የቤተሰብ ፈቃድ ከሣምንታዊ ክፍያዎ ላይ በ 60 % ላይ እንዲገደብ የተደረገ ሲሆን (የመጨረሻዎቹ የሥራባቸው 8 ሣምንቶች) ከፍተኛው ክፍያ $840.70/በሣምንት ይሆናል

## እንዴት አድርገው የሚያስፈልገውን ማሟላት እንደሚችሉ

የቤተሰብዎ አባል ክባድ የጤንነት ችግር ካለበትና ይህ ደግሞ ፈቃድ ባለው የጤና አገልግሎት ሰጪ ከተረጋገጠ ለኒው ዮርክ እስቴት (NYS) ተከፋይ የቤተሰብ ፈቃድ ሊያሟሉ ስለሚችሉ የሚከተሉትን መመሪያዎች ይከተሉ

• ሕጉን በሚመለከት የቤተሰብ አባል ማለት ባለቤት በቤት አብሮ የሚኖር ፓርትነር (ወዳጅ) (የአንድ አይነትና የተለያዩ ጾታዎችን ጥንዶችን ያጠቃልላል ሕጋዊ ምዝገባ አያስፈልገውም) ልጅ/የእንጀራ ልጅ እና ሕጋዊ አሳዳጊነት ያለብዎት ማንኛውም ልጅ  ወላጅ/የእንጀራ ወላጅ የባለቤት ወላጅ  አያት  ወይም የልጅ ልጅ

• ክባድ የጤንነት ችግር ማለት ሕመም ጉዳት ጉድለት የአካል ወይም የአእምሮ ችግር ያለበት ሆኖ በሆስፒታል በሆስፒስ ወይም ደግሞ በጤና እንክብካቤ መስጪያ ውስጥ ቆይቶ መታከም የሚያስፈልገው ወይም በጤና እንክብካቤ ሰጪ ተከታታይ ሕክምና ወይም ክትትል የሚያስፈልጋቸው ከሆነ

• ፈቃድ ያለው የጤና አገልግሎት ሰጪ የሚለው የሚከተሉትን ያጠቃልላል   ዶክተር የዶክተር ረዳት ካይሮፕራክተር የጥርስ ሐኪም  ፊዚካል ቴራፒስት ነርስ (practitioner)  ነርስ (registered) የእግር ሐኪም የዓይን ሐኪም ሳይኮሎጂስት ክሊኒካል ሶሻል ዎርከር የሞያ ደህንነት ቴራፒስት አዋላጅ የአእምሮ ጤና ሠራተኛ የንግግር - ቋንቋ ፓቶሎጂስቶች ኦዲዮሎጂስቶች ሆነው በሚሠሩበት የሞያ ዘርፍ አስፈላጊውን ሠነዶች የሚሞሉ ከኒው ዮርክ ውጪ ያሉና ከአሜሪካንም ውጪ ያሉም ጭምር የጤና እንክብካቤ ስጪዎች የሠራተኛውን የተከፋይ የቤተሰብ ፈቃድ ከሕክምና ጋር በተያያዘ ምክንያት አስፈላጊነቱን የሚያረጋግጡ ከሆነ ትክክለኛ የሆነ የሚሠሩበት እስቴት ወይም አገር ፈቃድ ኢንዲኖራቸው ያስፈልጋል

## እንዴት እንደሚያመለክቱ

### ልጅዎ ወይም የልጅዎ ትምህርት ቤት ተገልሎ ከሆነ

ከኢንተርኔት ላይ በዚህ ፓኬት ውስጥ ያሉትን ፎርሞች አውርደው ይሞላሉ: https://on.ny.gov/2xoPBYV

ይህንን ፎርም ለመሙላት የቋንቋ እገዛ የሚያስፈልግዎ ከሆነ በስልክ (844) 337-6303 ይደውሉና ከሚሰጡት አማራጮች ውስጥ 1 የሚለውን አማራጭ ይጫኑ ከዚያ ቀጥለው ደግሞ 5 የሚለውን አማራጭ ይጫኑ ኦፐሬተሩ በመለሰልዎት ጊዜ ኢንተርፕሬተር "Interpreter" በማለትና የእርስዎን ቋንቋ የእንግሊዝኛ ስም በመናገር አስተርጓሚ ይጠይቁ ኦፐሬተሩን ለማነጋገር ለረዥም ጊዜ በስልክ ላይ ሆነው መጠበቅ ያለብዎት ሲሆን በሚጠብቁበትም ጊዜ ብዛት ያላቸው በእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚሰጡ ማሳታወቂያዎች እንዳሉ እባክዎን ይገንዘቡ

ከላይ የተያያዙትን ፎርሞች በሚሞሉበት ጊዜ በፎርም PFL-1 ላይ ያሉትን 11ኛውንና 12ኛውን ጥያቄዎች አይመልሷችቸው ባዶ አድርገው ይተዋቸው እነዚህ ጥያቄዎች በዚያው በ ፒዲኤፍ (pdf) ፋይል ውስጥ ቀጥሎ በሚመጣው በSCOVID-19 ክፍል ውስጥ ተሸፍነዋል የሞሏቸውን ፎርሞች ቅጂ ለራስዎ ያስቀሩ ድንገት አሰሪዎ ለእርስዎ በሰዓቱ የማይመልስልዎት ከሆነ ይጠቅምዎታል  የተሞላውን ፎርም ለአሰሪዎ ይላኩ አሰሪዎ ፎርሙን በተቀበለ በ3 የሥራ ቀኖች ውስጥ የመመለስ ግዴታ አለበት

በመጨረሻም ፎርምዎን ለአሰሪዎችና ለሠራተኞች አካካሽ መድን ድርጅት ይላኩ አግኝተዋቸው ማመልከቻውን በኤሌክትሮኒክ መንገድ ይቀበሉ እንደሆነ ለማጣራት ይችላሉ ይማቀበሉ ከሆነ ግን በፖስታ ቤት በኩል መላክ ይኖርበታል  የአሰሪና የሠራተኞች ማካካሻ መድን ድርጅትዎን ለማግኘት የሚፈልጉ ከሆነ ከዚህ በታች ያለውን ማገናኛ ይጫኑ (ብዙ ገጾች ላይ መጫን ይኖርብዎታል) https://on.ny.gov/2QK1KP5

### የቤተሰብ እንክብካቤ

ከኢንተርኔት ላይ በዚህ ፓኬት ውስጥ ያሉትን ፎርሞች አውርደው ይሞላሉ: https://on.ny.gov/2wIXzMB
ይህ ፓኬት የሚከተሉትን ይይዛል፡

- የተከፋይ የቤተሰብ ፈቃድ መጠየቂያ (ፎርም PFL-1)
- የግል የጤና መረጃዎችን ከተከፋይ የቤተሰብ ሕግ ጋር በተያያዘ መልቀቂያ (ፎርም PFL-3)
- የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ሰጪ ከባድ የጤና ችግር ያለበትን የቤተሰብ አባል እንክብካቤ በሚመለከት የሚሰጠው አስረጂ (ፎርም PFL-4)

ፎርም PFL-1 ን ይሙሉ
ፎርም PFL-1 የተለያዩ ክፍሎች ያሉት ሲሆን በእርስዎ እና በአሰሪዎ የሚሞሉ ናቸው
የእርስዎን ክፍሎች ይሙሉና የሠነዱን ቅጂ ለራስዎ አስቀርተው ለአሰሪዎ በእጅ በፖስታ ቤት በኩል ወይም በኢሜይል ይስጡ  አሰሪዎ ፎርም PFL-1 ን በተቀበለ በ3 የሥራ ቀኖች ውስጥ ለእርስዎ የመመለስ ግዴታ አለበት አሰሪዎ ፎርሙን በሰዓቱ ካልመለሰልዎት የፎርም PFL-1ን እና የተቀሩትንም ፓኬጆች ቅጂ ለአሰሪዎች የመድን ድርጅት ይላኩ

ፎርም PFL-3 ን ይሙሉ
ፎርም PFL-3ን የሚሞላው የእርስዎ ቤተሰብ አባል (የእንክብካቤው ተጠቃሚ) ሲሆን ለጤና እንክበካቤ አገልግሎት ሰጪው ተሰጥቶ በፋይል የሚቆይ ነው  ይህ ፎርም የጤና እንክበካቤ አገልግሎት ሰጪው የቤተሰብዎን አባል ከባድ

የጤና ችግር መረጃ ለአሰሪዎ ኢንሹራንስ ድርጅት ለመልቀቅ ፈቃድ ይሰጠዋል  ይህንን ፎርም ለኢንሹራንስ ድርጅቱ እንዳይልኩት

ፎርም PFL-4 ን ይሙሉ
ፎርም PFL-4 የተለያዩ ክፍሎች ያሉት ሲሆን በእርስዎ እና በእርስዎ የቤተሰብ አባል የጤና እንክበካቤ አገልግሎት ሰጪ የሚሞሉ ናቸው የእርስዎን ክፍሎች ይሙሉና የሠነዱን ቅጂ ለራስዎ አስቀርተው ለጤና እንክበካቤ አገልግሎት ሰጪው ፎርሙን ይስጡት  አገልግሎት ሰጪውን የሚመለከታቸውን ክፍል በጊዜው ሞልተው እንዲመልሱልዎት ይጠይቋቸው

ለአሰሪዎ የመድን ድርጅት ይላኩ
ጥቅምዎን እንዳያጡ የሞሉትን የመጠየቂያ ፎርሞች ፓኬጅ ፈቃድዎን በጀመሩ በ30 ቀኖች ውስጥ ለአሰሪዎ የመድን ድርጅት መላክ ይኖርብዎታል  የፈቃድ ጥያቄዎን የሚደግፉ አስረጂ ሰነዶች በዚህ ቀነ ገደብ ውስጥ ለማግኘት ካልቻሉ የመድን ድርጅቱ ጥያቄዎን ውድቅ ሊያደርገው ይችላል  ፎርም PFL-1 እና ፎርም PFL-4 ከደጋፊ ሠነዶቻቸው ጋር ለአሰሪዎ የመድን ድርጅት ወይ በፖስታ ቤት  በኩል ወይንም በፋክስ ይላኩላቸው የአሰሪዎ መድን ድርጅት ማን እንደሆነ ለማወቅ የሚፈልጉ ከሆነ የአሰሪዎን ስም በመፈለግ የመድን ድርጅታቸውን ከዚህ በታች ያለውን ማገናኛ በመጠቀም ሊያገኙት ይችላሉ  የአሰሪዎችና የሠራተኞች ማካካሻ የመድን ድርጅት ለማግኘት ከፈለጉ ከዚህ በታች ያለውን ማገናኛ ይጫኑ (ብዙ ገጾች ላይ መጫን ይኖርብዎታል) https://on.ny.gov/2QK1KP5

የአሰሪዎን  የመድን ድርጅት ለማግኘት ካልቻሉ የተከፋይ የቤተሰብ የእገዛ የስልክ መስመር ላይ ዕርዳታ ለማግኝት በ 1 (844) 337-6303 ይደውሉና 1 የሚለውን አማራጭ ይጫኑ ከዚያ ቀጥለው ደግሞ 5 የሚለውን አማራጭ ይጫኑ ኦፐሬተሩ በመለሰልዎት ጊዜ ኢንተርፐሬተር “Interpreter” በማለትና የእርስዎን ቋንቋ የእንግሊዝኛ ስም በመናገር አስተርጓሚ ይጠይቁ ኦፐሬተሩን ለማነጋገር ለረዥም ጊዜ በስልክ ላይ ሆነው መጠበቅና በሚጠብቁበትም ጊዜ በእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚሰጡ በርካታ ማስታወቂያዎች እንደሚኖሩ እባክዎን ይገንዘቡ  የእገዛውን የስልክ መስመር ከሰኞ እስከ ዓርብ ከ 8:30 AM  እስከ 4:30 PM ለማግኘት ይችላሉ

አሰሪዎ የመድን ሽፋን እንደሌለው የሚያምኑ ከሆነ የተከፋይ የቤተሰብ ፈቃድ ጥያቄዎን ለኒው ዮርክ እስቴት (NYS) ሠራተኞች ማካካሻ ቦርድ በሚከተለው አድራሻ መላክ ይችላሉ

NYS Workers’ Compensation Board
Paid Family Leave
PO Box 9030,
Endicott, NY 13761-9030

## እንዴት ክፍያዎን እንደሚያገኙ

የመጀመሪያ ክፍያዎን ካገኙ በኋላ ተጨማሪ ክፍያዎች በየሁለት ሣምንቱ ይደረጋል  የመድን ድርጅቱ ክፍያውን እንዴት እንደሚከፍልዎት አማራጮች ሊሰጥዎት ይችላል ለምሳሌ በቀጥታ በባንክዎ አካውንት ውስጥ በማስገባት በዴቢት ካርድ (Debit card) ወይንም ደግሞ የወረቀት ቼክ በመስጠት ሊሆን ይችላል

እባክዎ ያስተውሉ  የተከፋይ የቤተሰብ ፈቃድ ክፍያዎች ታክስ ይከፈልባቸዋል  ከነዚህ ጥቅሞች ላይ ለታክስ መክፈያ ተብሎ በቀጥታ የሚያዝ ነገር የለም   ነገር ግን ሠራተኞች ይህንን በፈቃደኛነት በራሳቸው አነሳሽነት ለታክስ ተብሎ እንዲቆረጥለት ለመጠየቅ ይችላሉ በዚህ ክፍያ ላይ ያለውን የታክስ ክፍያ በመጨረሻ ላይ ታክስዎን በሚያስገቡበት ጊዜ የመክፈል ኃላፊነት አለብዎት

## የፌዴራል ተከፋይ የተስፋፋ የቤተሰብና የሕክምና ፈቃድ (የቤተሰቦች የመጀመሪያው የኰሮና ቫይረስ ምላሽ ውሳኔ የሠራተኛ ተከፋይ ፈቃዶች መብት (FFCRA))

FFCRA በ April 1, 2020 በሥራ ላይ ይውላል  FFCRA ወደኋላ በመሄድ የሚስተካከል የተከፋይ የሕክምና ፈቃድ አይደለም FFCRA እስከ 10 ሣምንቶች ተከፋይ የተስፋፋ የቤተሰብና የሕክምና ፈቃድ ለሠራተኛው ከመደበኛው ጠቅላላ ክፍያ  በ 2/3ኛ ስሌት መሰረት ይሰጣል ሠራተኛው በትንሹ ለ30 የካላንደር ቀኖች ተቀጣሪ ከነበረና ከCOVID-19 ጋር በተያያዙ ምክንያቶችና በቅንነት ትምህርት ቤቱ ወይም የጤና አገልግሎት ሰጪው ለተዘጋበት ልጅ እንክብካቤ ለማድረግ ሲባል ለመሥራት ባይችል ይህን ጥቅም ለማግኘት ያሟላል ይህ ከ50 በላይ እና ከ 500 በታች ባሏቸው ድርጅቶች ውስጥ ለሚሠሩ ሠራተኞች ይሆናል

ለፌዴራል ተከፋይ የሕመም ፈቃድ የሚያስፈልገውን ለማሟላት ከዚህ በታች ካሉት አንዱን ማሟላት ያስፈልግዎታል
• በተዕዛዝ ለተገለለ ሰው እንክብካቤ እየሰጡ ከሆነ
• ከCOVID-19 ጋር በተያያዙ ምክንያቶች ትምህርት ቤቱ ወይም የእንክብካቤ ሰጪው ለተዘጋበት (ወይም የልጅ የእንክብካቤ ሰጪ ሊያገኝ አልቻለም) ልጅ እንክብካቤ እየሰጡ ከሆነ

ለተገለለ ወይም በጤና አገልግሎት ሰጪ እራሳቸውን እንዲያገሉ ለተደረጉ ግለሰቦች እንክብካቤ የሚሰጡ ሠራተኞች የሙሉ ሰዓት ሠራተኞች እስከ 80 ሰዓቶች ዕረፍት ለማግኘት ይችላሉ የትርፍ ሰዓት ሠራተኛ ዕረፍት ለማግኘት ሠራተኛው በአማካይ በሁለት ሣምንቶች ጊዜ ውስጥ የሚሠራቸውን የዕለፍት ሰዓቶች ያገኛል

ትምህርት ቤታቸው ወይም የቀን መዋያቸው ከCOVID-19 ጋር በተያያዘ ምክንያት የተዘጋባቸውን ልጆቻቸውን ለሚንከባከቡ ሠራተኞች የሙሉ ሰዓት ሠራተኞች እስከ 12 ሣምንቶች ዕረፍት ለማግኘት ይችላሉ (2 ሣምንቶች ተከፋይ የሕመም ፈቃድና ከዚያ ቀጥሎ ደግሞ እስከ 10 ሣምንቶች ተከፋይ የተስፋፋ የቤተሰብና የሕክምና ፈቃድ) የትርፍ ሰዓት ሠራተኛ በጊዜው እንዲሠራ ይደረግ የነበረውን ሰዓቶች መሠረት ዕረፍት ለማግኘት ይችላል

## እንዴት ክፍያዎን እንደሚያገኙ

የፌዴራል ተከፋይ የቤተሰብ ፈቃድ ክፍያ በቀጥታ በአሠሪዎ በኩል ይከፈላል ለሁሉም መስፈርቱን የሚያሟሉ ሠራተኞች የፌዴራል ሕጉን ፍላጎት አሟልቶ ለመገኘት በጣም ቀላል ነው  ለቤተሰብዎ የጤና አገልግሎት ከሚሰጡ የሚጻፍ አስረጂ ክፍያውን ለመጠየቅ በቂ ሠነድ ነው ወይም ደግሞ የልጅዎ ትምህርት ቤት በግዳጅ በተደረገ ወይም ለቅድመ ጥንቃቄ ሲባል በተደረገ ማግለል ቢዘጋ ይህ ራሱ በቂ ነው

እባክዎ የሚከተለውን ይገንዘቡ  አፈጻጸም ላይ አሰሪዎችን የትኛው ሕግ እንደሚመለከታቸው ብዙ ግራ መጋባት ሊኖር እንደሚችል ይጠበቃል  መልሱ የተጣራ ገቢንና የሠራተኞችን ብዛት የሚመለከት ይሆናል ከ 50 እስከ 500

ሠራተኞችን ለሚያሰራ ድርጅት የፌዴራል ሕጉ የሚመሳሰሉ ጥቅሞችን ነው የሚሰጠው ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ የማመልከት ብቃትን አሟልቶ ለመገኘት ቀላል ነው   የፌዴራል እና የእስቴት መመሪያዎቹን ለአሰሪዎቻችሁ አሳይታችሁ የትኛውን ፕሮግራም ኀላፊነት እንዳለባቸው እንዲገነዘቡ ማድረግ ይኖርባችሁ ይሆናል

የፌዴራል መምሪያ ለአሰሪዎች: https://bit.ly/2UiNVt7
የእስቴት መምሪያ ለአሰሪዎች: https://on.ny.gov/2WMrLkA

## የፌዴራል ማነቃቂያ (stimulus) ቼኮች

ብዙዎቹ ያላገቡ ለአቅመ አዳም የደረሱ ግለሰቦች $1,200 የአንድ ጊዜ ክፍያ ያገኛሉ በተጨማሪ $500 ከ 17 ዓመት በታች ለሆኑ ጥገኛ ልጆች ይሰጣል  ልጆች የሌሏቸው ባለትዳሮች (ጥንዶች) $2,400 ያገኛሉ

ለማሟላት:

- ትክክለኛ የሆነ የሶሻል ሴኪዩሪቲ ቁጥር መኖርና በአሜሪካ ውስጥ ለመሥራት ፈቃድ ያለው መሆን
- ያላገቡ ለአቅመ አዳም የደረሱ ግለሰቦች ገቢያቸው ከ$75,000 በታች መሆን
- የቤተሰብ አስተዳዳሪ በሚል የተመዘገቡ ታክስ ከፋዮች ገቢያቸው ከ$112,500 በታች መሆን
- ባለትዳሮች (ጥንዶች) ሆነው ጥገኛ ልጆች ከሌሏቸው ገቢያቸው ከ$150,000 በታች መሆን

ገቢያቸው ከነዚህ ደረጃዎች በላይ የሆኑ የማነቃቂያ ቼኮች ሊያገኙ ይችላሉ  ነገር ግን ይህ የሚሆነው በአነስተኛ ደረጃ ይሆናል የ 2018 ና የ 2019 ገቢዎችዎ በጣም ከፍተኛ ከነበሩና በ 2020 ገቢዎ የሚቀንስ ከሆነም ያሟላሉ

ይህንን ክፍያ ለማግኘት ማመልከት አይኖርብዎትም የ 2018 ወይም የ 2019 ታክስ አስገብተው ከሆነና የፖስታ መላኪያ አድራሻዎና የባንክ መረጃዎ ካልተቀየረ ክፍያውን በ April 24 ያገኛሉ  ማንኛውም ለክፍያው የሚያሟላ ሁሉ ለየብቻው የማነቃቂያ ቼኩ መላኩንና ሌላም የክፍያውን መረጃ የያዘ ማስታወቂያ ይደርሰዋል

የ2018ን ታክስ ያላስገቡ ከሆነ የማግኘት ብቁነትዎንና ወይም ቼኩን የሚያገኙበትን ፍጥነት ሊጫነው ይችላል አንዱ ምክር የ2019 ትክስዎን ማስገባት ነው ምንም እንኳን ታክስ ማስገባት ባያስፈልግዎትም

የሶሻል ሴኪዩሪቲ የጡረታና የአካል ጉዳተኞች ክፍያ የሚቀበሉ ከሆነ ቬቴራን ከሆኑ ወይም ሥራ የሌለዎትም ቢሆኑ ይህንን የማነቃቂያ ቼክ ለማግኘት ያሟላሉ

እነዚህ የማነቃቂያ ቼኮች ታክስ አይከፈልባቸውም

## አደገኛ ሥራን ያለመሥራት መብት

ሠራተኞች አደገኛ ሥራን ላለመሥራት ሁለት ጥበቃ ያላቸው አማራጮች አሏቸው  ጥበቃ ያለው የተቀናጀ እንቅስቃሴና OSHA አደገኛ ሥራን ያለመቀበል መብት  ሠራተኞች በአሁኑ ጊዜ የተቀናጀ እንቅስቃሴን ጥበቃዎች በተሳካ ሁኔታ COVID-19ን በሚመለከት የሥራ ሁኔታዎችን ለማሻሻል ተጠቅመውባቸዋል ይህም በሚያስፈልግበት ጊዜ አደገኛ ሥራን ያለመቀበልን ያጠቃልላል የOSHA አደገኛ ሥራን ያለመቀበል መብት ብዙውን ጊዜ ገዳቢ ሆኖ ይታያል

## የተጣመረ እንቅስቃሴ

የተጣመረ እንቅስቃሴ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ አብረው የሚሠሩ ሠራተኞች በሚሠሩበት የሥራ ቦታ ለውጦችን ለማምጣት በሚነጋገሩበት ወይም በሚማከሩበት ጊዜ ይሆናል የተጣመረ እንቅስቃሴ ደህንነትን ያልጠበቀ የሥራ ሁኔታን ወይም የሕግ ጥሰትን ለእስቴት ወይም ለፌዴራል መንግሥቶች ማሳወቅን ሊያጠቃልል ይችላል እንቅስቃሴው አብረው ለሚሠሯቸው ሠራተኞች ሁሉ የሚጠቅም ከሆነ አንድ ሠራተኛ ብቻውን ቢሆን እንኳን በተጣመረ እንቅስቃሴ ሊሳተፍ ይችላል የተጣመረ እንቅስቃሴ ብዙ ነገሮችን ያጠቃልላል ደህናነትን አደገኛ ሥራዎችን ያለመቀበልንም ያጠቃልላል የተጣመረ እንቅስቃሴን በሚመለከት ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ የ WNYCOSHን ዌብሳይት ይመልከቱ: https://wnycosh.org/concerted-activity/ በተቻለ መጠን በተጣመረ እንቅስቃሴ ከመሳተፍዎ በፊት WNYCOSHን ወይም ደግሞ የሠራተኛ ጠበቃ ያማክሩና እንቅስቃሴው መስፈርቱን ማሟላቱን ያረጋግጡ

## የOSHA አደገኛ ሥራን ያለመቀበል መብት *

እርሶን ለአደገኛ ሁኔታ የሚያጋልጡ ሥራዎችን ወይም የተሰጡት ተግባሮች ለአደገኛ ጉዳት ወይም ለሞት የሚያጋልጡዎት ከሆነ ላለመቀበል ይችላሉ በዚህ በኩል ጥበቃ ለማግኘት ሠራተኞች ከዚህ ቀጥሎ ያሉትን ሁኔታዎች በሙሉ ማሟላት ይኖርባቸዋል

- በሚቻለው ሁሉ አሰሪዎን እንዲያስወግድ ይጠይቁና አሰሪዎ ይህንን ሳያደርግ ቢቀር እና
- ሥራውን ላለመቀበል የወሰኑት በትክክለኛ እምነት እንደሆነ  ይህም ማለት በእርግጠኛነት የማይቀርና ግልጽ የሆነ አደጋ እንዳለ ያምናሉ እና
- ትክክለኛ አስተሳሰብ ያለው ሰውም እውነተኛ አደጋ ወይም ከባድ ጉዳት እንዳለ ይስማማል እና
- በአደጋው አጣዳፊነት ምክንያት የተነሳ ሁኔታውን በመደበኛ የማስፈጸሚያ መስመሮች በኩል OSHA እንዲመረምር ለማድረግና ለማስተካከል በቂ ጊዜ የለም

ሠራተኞች ምንም ዓይነት ትክክለኛ አማራጭ ሳይኖራቸው በትክክለኛ ዕምነት የተነሳ ራሳቸውን ለአደገኛ ሁኔታ አናጋልጥም በማለት ሥራቸውን ባይቀበሉ ከአድልኦ ጥበቃ ይኖራቸዋል  እባክዎ የሚከተለውን ይገንዘቡ ይህን ለማስፈጽም በጣም አስቸጋሪ የሆነ ጉዳይ ነው በዚህም ምክንያት ሠራተኞች መብታቸውን ለማስከበርና ለማረጋገጥ ሲሉ ከሥራቸው ተባረዋል ሕይወትዎ ለማይቀርና ግልጽ ለሆነ አደጋ የተጋለጠ ከመሰለዎት እኛን የWNYCOSHን የሠራተኞች ማዕከል ስልክ መስመር (716) 206-3550 በመደወል ያግኙን  መለእክቶቹን በሥራ ሰዓቶች በቅርብ የምንቆጣጠራቸው ስለሆን አጣዳፊ ለሆኑ ጥያቄዎች በአንድ ሰዓት ውስጥ መልስ እንሰጣለን

*OSHA 29 CFR §1977.12(b)(2) ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት ማንኛውንም መብት መጠቀም

## ዋቢ

የቤተሰቦች የመጀመሪያው የኰሮና ቫይረስ ምላሽ ውሳኔ የሠራተኛ ተከፋይ ፈቃዶች ሕግ (FFCRA)
https://www.dol.gov/agencies/whd/pandemic/ffcra-employee-paid-leave

የተሻሻለ ምመሪያ 3/27/20:
https://www.dol.gov/newsroom/releases/whd/whd20200327

ተደጋግመው የሚነሱ ጥያቄዎች:
https://www.dol.gov/agencies/whd/pandemic/ffcra-questions

ለአሰሪዎች ፋክትሺት:
https://www.dol.gov/agencies/whd/pandemic/ffcra-employer-paid-leave

የኰሮና ቫይረስ ዕርዳታና የኤኮኖሚ ሴኪዩሪቲ ሕግ (CARES Act):
https://www.politico.com/f/?id=00000171-1429-d270-a773-777f92a00000

የNELP የCARES Act ትንታኔ
https://www.nelp.org/publication/unemployment-insurance-provisions-coronavirus-aid-relief-economic-security-cares-act/

ኒው ዮርክ ታይምስ ተደጋግመው የሚነሱ ጥያቄዎች (FAQ)
https://www.nytimes.com/article/coronavirus-stimulus-package-questions-answers.html

የኒው ዮርክ እስቴት (NYS) የሠራተኛ ክፍል የሥራ አጥነት ኢንሹራንስ
https://labor.ny.gov/unemploymentassistance.shtm

የኒው ዮርክ እስቴት (NYS) ተከፋይ የሕመም ፈቃድ:
https://paidfamilyleave.ny.gov/if-you-are-quarantined-yourself

የኒው ዮርክ እስቴት (NYS) ተከፋይ የሕመም ፈቃድ (የተገለለ ልጅ ላለው):
https://paidfamilyleave.ny.gov/COVID19

የኒው ዮርክ እስቴት (NYS) ተከፋይ የሕመም ፈቃድ እንዴት የመገለል ተእዛዝ እንደሚያገኙ:
https://paidfamilyleave.ny.gov/system/files/documents/2020/03/obtaining-order-of-quarantine.pdf

በ CDC COVID-19ን በሚመለከት ለየአገሩ የተሰጠ የመንገድ አወሳሰድ ምክር:
https://www.cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/travelers/map-and-travel-notices.html

የኒው ዮርክ እስቴት (NYS) ተከፋይ የቤተሰብ እንክብካቤ:
https://paidfamilyleave.ny.gov/paid-family-leave-family-care

የኒው ዮርክ እስቴት (NYS) ተከፋይ የቤተሰብ ፈቃድ COVID-19 ተደጋግመው የሚነሱ ጥያቄዎች (FAQ):

ይህ ገጽ ባዶ እንዲሆን የተደረገ ነው

## ለተጨማሪ መረጃ
## እባክዎ ያግኙን:

የWNYCOSH የሠራተኞች ማእከል የስልክ መስመር
(716) 206-3550

ይህ መመሪያ ሲዘጋጅ የሚከተሉት ረድተዋል:
ሴናተር ቲሞቲ  ኤም ኬኔዲ

የትርጉም ትባባሪዎች:
የተባበሩት የብረት ሠራተኖች (የስፓኒሽ ትርጓሜ)
የበፋሎ ባንግላ ጋዜጣ (የቤንጋሊ ትርጓሜ)
ሄን ቴት ዛት ሳው (የበርሚዝ ትርጓሜ)